


በ: ታማር ዛክስ
ምሳሌዎች: ዮሲ አቡላፊያ
הוֹצָאָה: מ' מזרחי
የእድሜ ክልል: መዋዕለ ሕጻናት

שִׂיחָה

**የጠፉ እቃዎችን መመለስ**

ኢ.ታማር ላይ እንደደረሰው የእርስዎ ወይም የሌላ ሰው የሆነ ነገር አጥተው ያውቃሉ? እቃው እንደጠፋ ሲያውቁ ምን ተሰማዎ? ሌላ ሰው ያጣውን ነገር እንዲፈልግስ ረድተዋል? የሌላ ሰው የጠፋ ነገር ሲያገኙስ ምን ይሰማዎታል? ይህስ ?በሚሆንበት ጊዜ ምን ማድረግ ይችላሉ

קְרִיאָה

**በምሥሎች ጉዞ ማድረግ**

በምሥሎቹ አማካኝነት ከሺህ ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት በእሥራኤል ምድር ስላለው ሕይወት ተጨማሪ ዝርዝሮችን ማግኘት ይችላሉ። በእያንዳንዱ ጊዜ በተለየ አስደሳች ዝርዝር ላይ ማተኮር ይችላሉ። ለምሣሌ:- የድንጋይ ቤቶች፣ እቃዎች ወይም እንስሳት ላይ ጥያቄዎችን መጠየቅና በሜዳ ላይ በግ ማሰማራት ምን እንደሚመስልና በሊቀ ካህናቱ ኮት ላይ ያሉት ደወሎች ምን እንደሚመስሉ ለማሰብ ይሞክሩ።

מִשְׂחָק

?ደወሉ የተደበቀው የት ነው

ደወልን ወይም ተመሳሳይ ነገርን በቤቱ ዙሪያ በመደበቅ መላውን ቤተሰብ በፍለጋ ማሣማራት ይችላሉ። ቀጥተኛ ያገኘው ሰው በሚቀጥለው ዙር የሚደብቅ ይሆናል። ለማግኘት አስቸጋሪ ከሆነስ? የተደበቀውን የደወል ድምጽ በማሰማት (እንደ "ግሊን ግሊን" ዓይነት) ለፈላጊዎቹ እንዲጠቁም መጠየቅ ይችላሉ። ጠያቂዎቹ ወደ ደበቀበት ቦታ በቀረቡ ቁጥር የደበቀው ሰው ደወሉን ያሠማል።

מִשְׂחָק

"የይገባኛል ጥያቄ የሚያቀርቡበት ድንጋይ"

ታኑ ራባናን፡- በኢየሩሣሌም የይገባኛል ጥያቄን የሚያቀርቡበት ድንጋይ ነበረ። የጠፋ ዕቃ ያለው ሁሉ ወደዚያ (ይመጣል። የጠፋ ዕቃም ያገኘም ሁሉ ወደዚያ ያመራል። (የባቢሎን ታልሙድ፣ ባባ ሜጺዓ ገጽ 28፣ ዓምድ 2

ከቤተሰቡ አባላት አንዱ "ፈላጊ" ይሆናል። እርሱም "የይገባኛል ጥያቄን በሚያቀርቡበት ድንጋይ" ላይ ቆሞ በቤቱ ውስጥ የተገኘን ነገር በዝርዝር ይገልፃል። በትክክል የገመተና ዕቃው ምን እንደሆነ የሚያውቅ ሰው የይገባኛል ጥያቄን ወደ ሚያቀርቡበት ያመጣውና ቀጣዩ የይገባኛል ጥያቄን የሚያቀርቡበት ድንጋይ ይሆናል።

שְׁמַע

**QR ኮድ**

ኮዱን ስካን ያድርጉና ታሪኩን በፒጃማ ቤተ መጻህፍት ትራክት ውስጥ ያዳምጡ።

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org